ERICSSON

# የመውጫና የመስሪያ ከፍታዎች

Standard

**ይዘቶች**

1 **መግቢያ** ... 3

2 **ኃላፊነቶች** ... 3

2.1 አስተዳደሮች ... 3

2.2 ተቀጣሪዎች ... 3

3 **መስፈርቶች** ... 4

4 **ጣቢያ እና የጣቢያ አስተዳደር** ... 5

4.1 ህንጻዎች እና ሰገነቶች ... 5

4.2 አንቴና የሚደግፉ መዋቅሮች ... 5

4.3 መጣያ ክልሎች ... 5

4.4 አሉታዊ የአየር ሁኔታዎች ... 6

4.5 ብርሃን ነክ ሁኔታዎች ... 7

4.6 ውስን የድንገተኛ ጊዜ ዝግጅቶች ... 7

4.7 የግንባታ ፋብሪካ መሳሪያዎች ... 7

5 **የግል መጠበቂያ መሳሪያ** ... 8

6 **የህክምና ብቃትና ምላሽ** ... 9

7 **የስጋት ጥናት እቅዶች** ... 9

8 **ቁጥጥርና ክለሳ።** ... 10

9 **መረጃ ቀይር** ... 10

© Ericsson AB 2021

መብቶች ሁሉ የተጠበቁ ናቸው።
በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ነው እንዲሁም ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊለወጥ ይችላል። ለማንኛውም እውነተኛ መረጃ መዛባቶች ወይም የትየባ ጽሁፍ ስህተቶች ኃላፊነት አይወስድም።

# 1 መግቢያ

ይህ ደረጃ ሁሉም የጤናና የደህንነት ገጽታዎች በአግባቡ እንደሚተዳደሩ ለማረጋገጥ ወደ ከፍታ ሲወጡና ሲሰሩ ሊሟሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ መስፈርቶችን ይገልጻል።

የአካባቢው ህግ እነዚህን መስፈርቶች የሚያልፍ ከሆነ የአካባቢው ህግ መስፈርቶች በተግባር ላይ ይውላሉ።

# 2 ኃላፊነቶች

## 2.1 አስተዳደሮች

ወደ ከፍታ የመውጣት መስተጋብሮችን የሚቆጣጠሩ አስተዳዳሪዎች ለመውጫዎችና ለከፍታ ስፍራ ስራዎች ለሚሆኑ መሳሪያዎችና ግብዓቶች ኃላፊነት ይወስዳሉ። አስተዳዳሪዎቹ የሚያረጋግጡት፡

- ከሚተገበረው ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማንኛውም ስጋቶች እንደተጠኑ እና በአግባቡ በቁጥጥር ስር እንደዋሉ
- ሴፍ ወርክ ሜትድ ስቴትመንትስ (SWMS) ለሁሉም የከፍታ ስፈራ መስተጋብሮች እንደሚተገበሩ
- ሁሉም የግንባታ መዋቅሮች ለመውጣት ደህና እንደሆኑ
- በከፍታ ላይ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ የሰለጠኑና የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው መሆኑን እንዲሁም ለሚተገብሯቸው ስራዎች ብቁ መሆናቸው ከታች በተገለጹት የብቃት ማረጋገጫዎች መሰረት፡

  የተፈቀደለት (መሰረታዊ) ከፍታ ወጪ ፡ የተወጠኑና የተወሰኑ የመገናኛ መስመሮችን የደህንነት መውጫ መሳሪያዎችን በመታጠቅ መውጣት የሚችል።

  ብቃት ያለው (ባለ ክህሎት) ወጪ።

- አቅራቦትን፣ ክምችትን፣ ምርመራን እና የ PPEን ደህና አጠቃቀም የሚያስተዳድሩ ስርዓቶችን እና
- መደበኛ የስራ አለባበሶች እንዲሁም መገናኛ መሳሪያዎች ተመቻችተዋል።

## 2.2 ተቀጣሪዎች

ሁሉም ተቀጣሪዎች፡

- ከተገለጹት ደህና የስራ ስርዓቶች ወይም የስጋት ጥናቶች የወጡ ሂደቶችን ለቅርብ ተቆጣጣሪ እና ለ Ericsson Global EHS Incident Reporting Tool ይዘግባሉ እንዲሁም

- ለመስመር አስተዳደሮቻቸው ክንውናቸውን ከመፈጸም የሚገቷቸውን ሁናቴዎች ይዘግባሉ

## 3 መስፈርቶች

የሚከተሉት መስፈርቶች ለማንኛውም ከሁለት ሜትር ወይም ከዛ በላይ ወደታች የመውደቅ ስጋት ላለው ስራ ይተገበራል፡

- እቅዶችና የስጋት ትናቶች በከፍታ ስፍራ ላይ ለሚሰሩ ተግባራት የተገበራሉ፤ ምዕራፍ 7ን ይመልከቱ።
- በከፍታ ስፍራ ላይ ስራ የሚከናውኑ ሰዎች ደረጃ ያለው ብቃት መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል (ከፍታ ወጪዎች ብቃት ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል) እንዲሁም ለሚሰሩት ስራ ተገቢ የሆነ የአካል ብቃት ያስፈልጋቸዋል። ተሃድሷዊ ስልጠና ወይም ዳግም ፈተና በአካባቢው ህግ መሰረት ይሰጣል ፤ ነገር ግን በምንም ዓይነት ሁኔታ ከሁለት ዓመት አይበልጥም።
- የግል የመከላከያ መሳሪያ ( PPE) ከመጠቀም በፊት በቂ የሆነ ስልጠና ለተጠቃሚውና ለተቆጣጣሪው የ PPE አጠቃቀምና ጥገናን በሚመለከት ይሰጣል። እንዲህ አይነቱ ስልጠና በሰነድ ይያዛል።
- ሁሉም የስራ መሳሪያዎች የ PPEን መስፈርቶች ለመሟላት በጥናት ላይ ይውላሉ፤ ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ።
- የጣቢያው ሀላፊ መዋቅሩ ለመውጣት አስተማማኝ መሆኑን ስራ ከመጀመሩ በፊት ያረጋግጣል።
- ማንኛውም የከፍታ ወጪ ማማዎችን፣ ምሰሶዎችን፣ የጠርዝ ማማዎችን ለመውጣት ወይም ሌላ ምንም ዓይነት የከፍታ በታ ስራ የአካባቢውን ስጋት ጥናት ሳይተገብር እንዲሁም ሌላ አንድ የማዳን ስልጠና የወሰደ የታጠቀ የከፍታ ወጪ በሌለበት እንዲወጣ አይፈቀድም።
- PPE ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ሊመረመር ይገባዋል፤ ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ።
- በተገቢው የመውጫ PPE የከፍታ ስፍራ ወጪዎች ከተፈቀደለት መልህቅ ጋር ወይም በመውደቅ ጊዜ ከሚያስር መሳሪያ ጋር ሁልጊዜ ከፍታ ሲወጡና ከተጠበቁስፍራዎች ውጪ ሲሰሩ መያያዝ ይኖርባቸዋል።
- በኤሌክትሮማግኔቲክ (RF) ስፍራዎች አካባቢ ሲሰሩ ስራው ደረጃ ካላቸው ‹‹ራዲዮ ፍሪኩዌንሲ እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ስፍራዎች ተጋላጭነት››መስፈርቶች ጋር መስማማት አለበት።
- በኤሌክትሪክ ዝርጋታ እና ሀይል መስመሮች ዙሪያ ሲሰሩ ከነዚህ መስመሮች ጋር ምንም አይነት አስተላላፊ ግንኙነቶች እንደማኖሩ ለማረጋገት ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል።

**ማስታወሻ፡** ምንም አይነት ‹‹ነጻ የከፍታ መውጣት›› አይፈቀድም። በነጻ ሲወጣ የተገኘ ማንኛውም ሰው በኤሪክሰን ቢዝነስ የሚሰራበትን የከፍታ ስፍራ መውጫ ፈቃዱን ያሰርዛል።

# 4 ጣቢያ እና የጣቢያ አስተዳደር

## 4.1 ህንጻዎች እና ሰገነቶች

የህንጻ አልም የሰገነት ጣቢያዎች በሚገበኙበት ሰዓት የስጋት ጥናቶች ተደርገው አስፈላጊዎቹ የቁጥጥር መለኪያዎች መተግበር አለባቸው። ኤሪክሰን አሁን ስላለው ጣቢያ የመገናኛ መብቶችን ጨምሮ የስጋት ጥናቶች ተጨማሪ መረጃዎችን ከተገኙ ማቅረብ ይችላል።

ሰራተኞች የስራ ቦታውን አካባቢያዊ የስጋት ጥናት ስራ ከመጀመሩ በፊት ይተገብራሉ ፤ ይህም የንጣፍ እይታ ምርመራ፣ ቋሚ የጥበቃ መከላከያዎችን ወይም ሌሎች የውድቀት ጊዜ መጠበቂያ እርምጃዎችን ጥቅም ላይ ከማዋላቸው በፊት እንዲያካቱ ነው። የስራ ስፍራውን ከስጋት ነጻ ለማድረግ ተመጣጣኝ ቅድመ ጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር በቀላሉ ሊፈራርሱ በሚችሉ ስፍራዎች አካባቢ መገኘትም ሆነ መስራት የተከለከለ ነው።

ጥበቃ ካልተደረገለት ጠርዝ በሁለት ሜትር ርቀት ውስጥ የሚካሄድ ስራ ሁሉ ሙሉ የሆነ የደህንነት ስርዓት ያስፈልገዋል። ለምሳሌ የጥበቃ መከላከያዎችን፣ የሴፍቲ ኔት ስርዓቶችን፣ የማስጠንቀቂያ መስመር ስርዓቶች፣ የደህንነት ቁጥጥር ስርዓቶች ወይም የግል የውድቀት ጊዜ ማሰሪያዎች ናቸው። አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የጥበቃ ስርዓቶች ሁልጊዜም ሰራተኞች ሁለተ ሜትር ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ከፍታ ለመውደቅ ተጋላጭ ሲሆኑ በቦታ መኖር አለባቸው።

## 4.2 አንቴና የሚደግፉ መዋቅሮች

ሁሉም የአንቴና ድጋፍ ሰጪ መዋቅሮች በአምራቹ ዝርዝር መመሪያዎች መሰረት ለሁኔታ ምርመራ ታልፈው ይሰጣሉ።

ከመውጣቱ በፊት ጊዜውን የጠበቀ፣ ለመውጣት ደህንነቱ የተረጋገጠ የሚል የብቃት ማረጋገጫ እንዳለውና የቅድመ መውጣት ምርመራ እንደተካሄደ ማረጋገጥ የከፍታ ስፍራ ወጪው ኃላፊነት ነው።

የከፍታ ስፍራ ወጪዎች ጥብቅ ትኩረት ለመዋቅሩ ሁኔታ ማድረግ አለባቸው፤ እንዲሁም ለስጋት መንስኤ የሆኑ ነገሮች በሚታዩበት ወቅት መውጣት ማቆም አለባቸው።

## 4.3 መጣያ ክልሎች

አንድ ‹‹መጣያ ክልል›› እቃዎች ወድቀው ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉበት በአንድ መዋቅር መሰረት ላይ ያለ ስፍራ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ይህን ስፍራ አመቺ የሆኑ ጊዜያዊ ከለላዎችን፣ ቆቦችን ወይም በበቂ ምልክቶች የታጀቡ ገመዶችን በመጠቀም መሬት ላይ ያሉትን ለመጠበቅ በግልጽ ማመልከት ያስፈልጋል። ስለአደጋው የሚያውቁ፣ የተፈቀደላቸውና የደህንነት ቆብ ያደረጉ ግለሰቦች ብቻ ወደ መጣያ ክልሉ እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል።

መጣያ ክልል በተባለ ቦታ ላይ አጎራባች ንብረቶች ከተቀመጡ ከጎረቤቶች ጋር ከፍታውን ከመውጣት በፊት በቅድሚያ የሚደረግ ተገግባቦት ያስፈልጋል።

አሞቺ ከለላዎችና ምልክቶች ወደ መጣያው ክልል መግቢያ ላይ አካባቢው የስጋት ጥናት መስፈርቶች መሰረት መቀመጥ አለባቸው።

የሚከተሉት መስፈርቶች ለከፍታ ስፈራ መውጣትና ለከፍታ ስፈራ ስራዎች ያገለግላሉ፡

- የሚወድቁ መገልገያዎችን እና መሳሪያዎችን ስጋት ለመቀነስ በተቻለ መጠን ከከፍታ ወጪው ሰው ማሰሪያ ጋር መታሰር አለባቸው (የተፈቀደለት የመልህቅ ቦታ ነው) አልያም በጥንቃቄ በተዘጋ ቦርሳ ውስጥ መግባት አለባቸው።

- እንደ ብሎኖችና ማሰሪያዎች ያሉ ጥቃቅን የማይታሰሩ ንብረቶች ባሉበት አማራጭ መንገድ ከመውደቅ የሚገታቸውን አማራጭ መንገድ  መጠቀም ይገባል። ለምሳሌ ጥልፍልፍ መረቦች ወይም ቦርሳዎች ከመስሪያው ቦታ በታች የሚወድቁ እቃዎችን ለመያዝ መዘርጋት ይችላሉ። ሁሉም አማራጮች ከግምት ወስጥ ገብተው እንዲሁም ተትተው ከሆነ እና ይህን ማድረግ አስተማማኝ ደህንነት ካለው የመጣያ ክልሉ የጉዳትን ስጋት ለመቀነስ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

- በሚያስፈልግበት ወቅት ንብረቶች በሽክም አልያም ዝቅ በማድረግ ከከፍታ ላይ ይወርዳሉ። በማናቸውም ሁኔታዎች ምንም አይነት እቃ ወደታች መወርወር አይቻልም።

- ተንቀሳቃሽ የከፍታ የስራ መድረክ ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ከፍታ  ወጪዎች ወደመስሪያ ስፍራቸው እየሄዱና እየተመለሱ በቅርጫቱ ወስጥ ታስረው ይቀራሉ።

- ተንቀሳቃሽ የከፍታ የስራ መድረክ እንደሰገነት መገናኛ ሲጠቀሙ የከፍታ ወጪዎች ቅርጫቱን የሚለቁት በጥብቅ እንዲሁም ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ በሰገነቱ ላይ ሲያርፍ ነው።

## 4.4 አሉታዊ የአየር ሁኔታዎች

አሉታዊ የአየር ሁኔታዎች በሚበረቱበት ጊዜ ከፍታውን የሚወጡ ሰራተኞች መውጣት ደህንነቱ የተጠበቀ አማራጭ መሆኑን ማጥናት ይኖርባቸዋል ። ይህ በተለይ የሚከተሉት የአየር ሁኔታዎች በሚገኙበት ጊዜ ይተገበራል፡

- አውሎ ነፋስ ወይም ከፍተኛ ውሽንፍር

- እጅግ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

- በረዶ ወይም የበረዶ ክምር በመዋቅሩ ላይ

- ኤሌክትሪክ ነክ ውሽንፍር በአካባቢው

- ከፍተኛ ዝናብ

- የበረዶ ግግር፣ የበረዶ ክምር አልያም በረዶ

- ከፍተኛ ወይም ፈጣን ነፋስ

- ደካማ የእይታ ሁኔታ

## 4.5 ብርሃን ነክ ሁኔታዎች

ዝቅተኛ የብርሃን መጠን በከፍታ ስፍራ ላይ መስራትን አስጊ ያደርገዋል። የአካባቢው የስጋት ጥናት ስራ እንዲጀምር ወይም እንዲቀጥል የማይፈቀድባቸውን ሁኔታዎች መግለጽ አለበት። እነዚህ ሁኔታዎች የሚያካትቱት ነገር ግን የማይወሰኑባቸው፡

- በተጠበቁ መንገዶች አማካኝነት ሊገኙ የማይችሉ የስራ ስፍራዎች (ለምሳሌ የውስጥ ደረጃዎች፣በውድቀት ጊዜ የሚያስር ስርዓት ያላቸው  በብረት የተዘጉ መሰላሎች
- ያለ ጠርዝ ጥበቃዎች ያሉ የስራ ስፍራዎች
- በቂ ያልሆነ ቋሚ መብራት በጣራዎች ላይ በሚቀርብበት ወቅት፤ እንዲሁም በቂ የግል ተንቀሳቃሽ መብራት ለመዋቅሮችና ለመሳሪያዎች ስራ በማይገኝበት ሁኔታ እንዲሁም
- ስራን አሁን ባለው መንገድ መቀጠል እስከ ማይቻልበት ደረጃ ድረስ የብርሃን ሁኔታዎች በሚቀንሱበት ጊዜ ነው።

በንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ብርሃን የስራ ስፍራውን ደህና ለማድረግ ያስፈልጋል። ይህም የራስ ላይ መብራት ለከፍታ ወጪ ሰራተኞች እንዲሁም በመሬት እና/ወይም የጥላን እና የነጸብራቅን ተጽዕኖ ለማስቀረት በመዋቅሩ ተገቢ ማስቀመጫ ስፍራዎች ላይ የሚደረጉ መብራቶችን ያካትታል።

የ‹‹ስጋት ጥናትና እቅዶች›› አቅራቦቶች ተዳስሰው ስምምነት ላይ ካልተደረሰባቸው በስተቀር ምንም አይነት የማንሳት እና የማውረድ ተግባራት አይከወኑም።

## 4.6 ውስን የድንገተኛ ጊዜ ዝግጅቶች

አንድ የከፍታ ስፈራ፣ ወጪ ሰራተኛ ራሱን ከሳተ እንዲሁም እሱን ማዳን ካልተቻለ በዙሪያው ያሉ ሌሎች የከፍታ ስፈራ ወጪ ሰራተኞች ከቻሉ እና ከስጋት ነጻ ከሆኑ ራሱን የሳተውን ሰራተኛ አቀማመጥ ማቅለል ይኖርባቸዋል።  በደም መላሽ ቧንቧ መዘጋት ምክንያት ሊከሰት የሚችል የሞት አደጋን ለማስወገድ የሚረዳው እስኪመጣ ድረስ አቀማመጡን የማቅለል ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀጠል አለበት

## 4.7 የግንባታ ፋብሪካ መሳሪያዎች

ሁሉም በከፍታ ስፍራ ላይ የሚሰራባቸው ወይም የማንሳትና የማውረድ ስራዎችን የሚሰሩ የግንባታ ፋብሪካ መሳሪያዎች የአካባቢውን ህጎችና ደረጃዎች ለፕሬተሮችና ለህዝብ ደህንነት ሲባል ማሟላት አለባቸው።

ይህ ቅድመ ሁኔታ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፣ ቅድመ ምርመራዎችን እንዲሁም የግንባታ ፋብሪካ መሳሪያዎችን ጥቅምና መስፈርቶች ያካተተ አቅራቦቶችን ይይዛል።

## 5 የግል መጠበቂያ መሳሪያ

የሚከተሉት የግል መጠበቂያ መሳሪያ ደረጃዎችን የሚያሟሉ የPPE እቃዎች ለሁሉም የከፍታ ስፍራ ወጪ ሰራተኞች ይሰጣሉ፡

**የደህንነት ማሰሪያዎች፡** ተገቢው የሙሉ አካል ማሰሪያ ለሁሉም የከፍታ ስፍራ ስራዎች የንዝረት ስቦ ማስቀሪያ መሳሪያ ካለው ገመድ ጋር ጥቅም ላይ ይውላል።

**ጫማዎች**: ማንኛውም ጫማ ከፍታን ለመውጣት ጥቅም ላይ ከዋለ በደንብ የሚስማማ፣ ውስጡ የጠነከረ፣ ብረት ለበስ የጣት መከላከያ እንዲሁም የተለየ የተረከዝ ማሰረፊያ ያለው ሊሆን ይገባል።

**ጓንቶች፡** ጓንቶች በቂ ጥንካሬ እና ሙቀት ያላቸው እንዲሁም እንቅስቃሴን የሚገቱ መሆን የሌለባቸው ናቸው።

**የከባድ አየር ሁኔታ አለባበሶች፡** የከባድ አየር ሁኔታ አለባበሶች በሚያስፈልጉበት ወቅት ጥቅም ላይ ይውላሉ። እነዚህ ልብሶች በቂ ጥንካሬና ሙቀት ያላቸው እንዲሁም ሙቀት የማያስገቡ መሆን አለባቸው።
እነዚህ ልብሶች፡

- ሲለበሱ እንቅስቃሴ መግታት የለባቸውም
- በነፋሻማ አየር ሁኔታ ልቅ የሆኑና እንደ ‹የመርከብ ጨርቅ› የሚሆኑ መሆን የለባቸውም
- ያልታሰሩ ማሰሪያዎች፣ ልጥጥ ቀበቶዎችና የቀበቶ ማሰሪያ ብረቶች ወይም ሌሎች ሊያዙ የሚችሉና
- ሌላ አብሮ ከ PPE ጋር የሚለበስ መሳሪያን አደጋ ላይ የሚጥሉ ልብሶች መሆን የለባቸውም።

**የራስ ከለላ፡** የከፍታ ስፈራ ወጪ ሰራተኞች የራስ ቆብን ያካተተ የራስ ከለላ ከተፈቀደው የዓለም አቀፍ ደረጃ የመጣ እንዲሁም የአገጭ ጋር ማሰሪያ ያለውና በሚያገለግልበት አካባቢ መሰረት የሚመረጥ መሆን አለበት ።

PPE እንደሚከተለው ይመረመራል፡

- በመጀመሪያ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት፡ መደበኛ የመመርመሪያ ሰነድ በአምራቹ በኩል ይቀርባል።
- በእያንዳንዱ ጊዜ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት፡ በከፍታ ስፍራ ወጪ ሰራተኛው የሚደረግ ምርመራ።
- ቢያንስ በየ12 ወሩ፡ ብቃት ባለው ሰው የሚደረግ ምርመራ ። (የደህንነት ጫማዎችን/ቦቲዎችን እንዲሁም ከባድ ኮፊያዎችን አያካትትም)።

## 6 የህክምና ብቃትና ምላሽ

በስራው ከፍታ አማካኝነት የትኛውም የጤናው ገጽታ በራሱ ላይ ሆነ በሌላው ላይ ስጋት እንደማያመጣ ለማረጋገጥ በየአካባቢው ህግ በሚፈቅድበት ጊዜ ሁሉ የከፍታ ስፍራ ወጪ ሰራተኛው የህክምና ጤና ምርመራ በየሁለት ዓመቱ እንዲያደርግ ይገደዳል።

ከህክምናው ጤና ምርመራ በኋላ ‹‹ለመውጣት ብቁ›› ተብለው ያላለፉ ወይም የመውጣት ችሎታቸው ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ ጊዜያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም ጉዳቶችን ያስተናገዱ ወጪ ሰራተኞች ከማንኛውም ዓይነት የመውጣት ስራ ይታገዳሉ።

## 7 የስጋት ጥናት እቅዶች

መውጣት እና/ወይም በከፍታ ላይ የመስራት ክዋኔዎች በስኬታማነት እንዲደረጉ አካባቢያዊ የስጋት ጥናቶች የትኛውም ስራ ከመጀመሩ በፊት ይተገበራሉ።

የወጪ ሰራተኞች መሪ ሃላፊነቱን እንዲወስድ ይመደባል። ግልጽ የአካባቢ ስጋት ጥናቶች የሚካትቱት ነገር ግን የማይወሰኑባቸው የሚከተሉት ናቸው፡

- የስራዎች/ክንውኖች ባህሪ
- የስራ በታው አቀማመጥ (የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገዶችን ለምሳሌ እሳት)
- ወደ ከፍታ መውጫ ጣቢያው መግቢያ እንዲሁም መውጫ
- የመጣያ ክልሎች
- የአየር ሁኔታ
- የማታ ስራ
- ከመጠን ያለፉ የሀይል መስመሮች
- የማንሳትና የማውረድ ኦፕሬሽኖች
- የአካባቢው ሁኔታዎች።

ጠቅላላ የስጋት ጥናቶች ቀድመው ሊታዩ የሚችሉ አደጋዎችን ለመለየትና ተመጣጣኝ የስጋት መቆጣጠሪያ እርምጃዎችን ለመቀመር ይጠቅማሉ። በተጨማሪ አካባቢያዊ የስጋት ጥናቶች ለሁሉም የከፍታ መውጣት ተግባራት፣ የከፍታ ስፍራ ስራዎች እንዲሁም የማንሳት ስራዎች መተግበር አለባቸው።

ጣቢያውን ከመጠቀምዎ በፊት ማንኛውም በቦታው ላይ ያሉ መዛግብቶችን ቀድመው የነበሩ የተዘረዘሩ አደጋዎችን ለማወቅ ማጣራት ያስፈልጋል።

የአካባቢው የስጋት ጥናት በሰነድ ይቀመጣል።

# 8 ቁጥጥርና ክለሳ።

ይህ ደረጃ መጠበቁን ለመቆጣጠር በመከለስና ጠቃሚ መዛግብቶችን በመጠበቅ እነሱም፡-

- የክስተት አሃዛዊ መረጃ፣
- የተሰጡ PPE እና ምርመራዎች
- የግንባታ ስራ ፋብሪካ መሳሪያዎች
- ‹‹ለመውጣት ብቁ›› የሚሉ የብቃት ማረጋገጫዎች
- የከፍታ መውጫ ብቃት ማረጋገጫ ዎችን ያካተቱ የስልጠና መዛግብት።

# 9 መረጃ ቀይር

1 የሀላፊነት ክፍል ተጨምሯል

2 ለክፍል4.1 ህንጻዎችና ሰገነቶች የተደረጉ ማሻሻያዎች